# ልዩነት !

በአንድ ሀገር ዜግነት
በኢትዮጵያዊነት
ስንኖር በአንድ ላይ
እኔ ከታች ሆኜ አንተ ከኔ በላይ
አንድ ነን ስትለኝ በእጅጉ ደንቆኛል
የብቻህ ዜግነት እኔን ያኮራኛል ?
ባንተ ቤት ነፃነት ተትረፍርፎ ሞልቶ
በኔ ቤት ባርነት ያለቅጥ ጎልብቶ
ባንተ ቤት ጥጋቡ
በኔ ቤት ረሃቡ !!

አንተ በልተህ ጠግበህ ሳድር እኔ ጦሜን
ምን ዓይነት ታምር ነው አንድ የሚያደርገን ?
ሁሉም ተንሠራፍቷል እንደ ስጦታችን
መፍትሄ ካልመጣ ለልዩነታችን
በኔ ተገዥነት ባንተ ጌትነት
ሕይወትን ልንዘልቃት በሁለት ዜግነት
ጌታው እንዳትሞኝ አይሆንም ይህ ነገር !
ውርድ ከራሴ ነው ዛሬ ይስማኝ ሀገር
በነገው ውድቀትህ !
በነገው ሽንፈትህ !
ጸጸት እንዳይገባህ ልቅሶህ እንዳይበዛ
ምክሬን እንዳታየው በዋዛ ፈዛዛ

እኔ አይደለሁ አንተን
አንተ እንዴት እኔን ?
በመልክ በጸባይ ባስተሳሰባችን
ልዩነት አለን
በዘረ-ብዙነት አንድ ብንመስልም
የትውልዱን ጥምረት ሕዝብ ቢያምንበትም
አንተ ግን ክደሃል !
ከመስመር ወጥተሃል !
ሳይዘራ-በቀል እንክርዳድ ሆነሃል !!
ሕዝቡ አውግዞሃል !
ታሪክም ተፍቶሃል !
በአውሬነት ባኅሪኅም ዓለም ታዝቦሃል !
ቆመህ ሣያምርብህ
ሞተህ ሳያምርብህ
ለከርሠ መቃብር ምድር ጠርታሃለች
ዓለም ልትረሳህ ተዘገጃጅታለች ::

ይህ ጊዜ ይለወጣል አይለወጥ መስሎህ
በጎሣ ሠንሰለት ታሥረህ ትቃዣለህ !
ስለዚህ ልንገርህ ዕውነቱን ስማኝ
አንድ ነን በማለት አትሸንግለኝ !
እኔ መኖር ስሻ ሞት ፈርደህብኝ !
ሥቃይን ስቀበል በነፍስና አካሌ
በምን ተምሳሊት ነው እኔ አንተን መምሰሌ ?
ሰው በመሆናችን ብንመሳሰልም
ኑሮና ባኅሪያችን አንድ አያደርገንም
ዓለም ላንተ ጣፍጣ ለኔ ስትመረኝ
ሰው በመባል ብቻ አንተን አታርገኝ

ላንተ የሚጣፍጠው ሲመረኝ እኔን
በቅምሻ ላይ እንኳ ልዩነት አለን !!!
እኔ ፍቅርን ስሻ አንተ ጥላቻን
እንዴት ይጣጣማል ሃሳብ ግብራችን ?
እኔ በዚህ ስሄድ አንተ በዚያኛው
መንገዳችን እንኳ ልዩነት አለው !
ትርጉሙ ይኸው ነው ሁለት ዜግነት
የኔ ጭቁንነት ያንተ ጌትነት
ጥቂት እንጥፍጣፊ ካለህ ተስተውሎ
ቆም ብለህ እየው የዋልኸውን ውሎ
ያሸነፍህ መስሎሃል
ግን ተሸንፈሃል !
የከበርህ መስሎሃል
ግን ድሃ ሆነሃል !
ብልጥ ነኝ ብለሃል ፤
በደም ነግደሃል
ነገ ባዶ ቤት ነህ ኪሣራ በልቶሃል !

ሕዝቡ ትዕግሥቱ አልቆ ቂም-በቀሉ ነዶ
ምድር ቀውጢ ሆና ሁሉም ሆኖ ባዶ
የተመካህበት ሀብትህም ተንዶ
በጸጸት በልቅሶ ወይ ነዶ ወይ ነዶ
ወንዝ አያሻግርም ከዚህ እዚያ ማዶ
ለመሠሪው ሥራህ አንተን ያጀቡህም
አሽከሮችህና ኃያል ጌቶችህም
በፈጸማችሁት ታላቅ በደላችሁ
በእግዜርም በሰው ፊት ተጠያቂ ናችሁ
ምከረው ምከረው
ፊጽሞ ካልገባው .........
ይፈጸማል ቃሉ አበው ያሉት አይቀር
ፍርዱን ታየዋለህ እንዳትጠራጠር !!